# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 170 ነሃሴ 12 2003 ገጽ 1


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የታሪክ አነባበብ ልዩነት በሃገራች አንድነት ላይ የደቀነብንን ፈተና መወጣት የኛ - ማለትም የዚህ ዘመን ትውልድ - ኃላፊነት ነው ብሎ ያምናል። በዚህ እምነቱ መነሻም በ2010 እ.አ.አ. ባሳተመው "ነፃነት፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲና አንድነት" በተሰኘው መጽሃፉ ውስጥ ስለአገር አንድነት በአጠቃላይ፤ በተለይ ደግሞ ስለታሪክ አነባበብ ልዩነት፤ ይህ ልዩነት የሃገራችንን አንድነት አደጋ ላይ መጣሉን እና መፍትሄውም ምን እንደሆነ ሰፋ ያለ ትንተና አቅርቧል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአገራችን ተደጋግሞ የሚከሰተው ረሃብ መንስኤ ሰው ሰራሽ መሆኑን የዓለም ባንክ አጋለጠ

ሮይተርስ በመባል የሚታወቀው ታላቅ የዜና አውታር ባወጣው ዘገባው ኢትዮጵያን በዋነኛነት ያጠቃለለው የምስራቅ አፍሪቃው የርሃብ ችግር ዋነኛ መንስኤው ሰው ሰራሽ መሆኑን የዓለም ባንክ ማስታወቁን ገልጹአል:: እንደ አለም ባንክ ገለጻ በምስራቅ አፍሪቃ ሃገራቱ እየታየ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ማሻቀብ፣ የሲቪል ማህበረሰቡ አለመረጋጋትና የተለያዩ ብጥብጦች መሆናቸውን አስታውቁአል::

በምስራቅ አፍሪቃ ለታየው ድርቅ ዋና መንሴው ሰው ሰራሽ ችግር መሆኑን የተናገሩት በአለም ባንክ ከፍተኛ የኢኮኖሚክስ ባለሙያ የሆኑት ወልፍ ጋንግ ፌንግለር ሲሆኑ ለሮይተርስ የዜና ወኪል በቴሌፎን ባደረጉት ቃክለ ምልልስም የዚህ የምስራቅ አፍሪቃ ሃገራት ቀውስና ረሃብ መንስኤው ሰው ሰራሽ ችግር ለመሆኑ ምንም የሚያጠያይቅ አይደለም:: የድርቅ ችግር ዛሬ የተከሰተ ሳይሆን ለረጂም አመታት ወቅት እየጠበቀ በተወሰኑ አመታት የሚመጣ እንደሆነ ይታወቃል:: ነገር ግን በየሃገራቱ ያለው የፖሊሲ ችግር ይህን የድርቅ ችግር ወደ ከፋ ረሃብ እንዲሸጋገር አድርጎታል ብለዋል:: ከዚሁ ጋር በማያያዝ ፌንግለር እንደተናገሩት ለምሳሌ ያህል ባሁኑ ሰአት የበቆሎ ዋጋ ከሌሎች የአለማችን ሃገራት ጋር ሲነጻጸር በነኝህ የምስራቅ አፍሪቃ ሃገራት ዋጋው እጂግ ከፍተኛ እንደሆነ መረጃ በማስደገፍ ተናግረዋል:: እንዲህ አይነቱ የዋጋ ማሻቀብ ደግሞ የየሃገራቱን የገበያ ዋጋ ግሽበት ያባብሳል ብለዋል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት እየወደመ ነው፣ በአባይ ሸለቆ ላይ የሚደርሰው ጥፋት እንደቀጠለ መሆኑ ታወቀ

በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የጥፋት ዘመቻ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት እየወደመ ሲሆን ማእድን ለማውጣት በሚል በአባይ ሸለቆ ላይ የሚደርሰው ጥፋት እንደቀጠለ መሆኑን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘጋቢዎቹን ዋቢ በማድረግ ገለጸ::

በተለምዶ የአባይ በረሀ እየተባለ የሚጠራውን አካባቢ በመጎብኘት ዘገባ ያጠናቀሩት የኢሳት ጋዜጠኞች እንደገለጹት የሙስና እናት በመባል በምትታወቀው የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን እህት ልጅ የሚመራው ወርኪድስ ድርጅትና ሌሎችም በማእድን ስራ ማውጣት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ሀላፊነት በጎደለው ሁኔታ የሚያካሂዱት ቁፈራዎች የአካባቢውን ተፈጥሮ እያዛባ መሆኑ ታውቁአል።

የኢሳት ዘጋቢዎች አክለው እንደገለጹት በላይምስቶን ማእድን ፍለጋ ላይ ከፍተኛውን ስራ የሚሰራው የአዜብ መስፍን እህት ልጅ ወርኪድስ ድርጅት የሚያደርሰው ጥፋት ለማንም ታዛቢ በግልጽ የሚታይና እጂግ አሳሳቢ ሁኔታንም እየፈጠረ ያለ ተግባር ነው።

አካባቢው ቀደም ብሎ ምድረበዳ ወደ መሆን ደረጃ እየተሸጋገረ የነበረው የአባይ ሸለቆ በዘረኛው አገዛዝ የዘፈቀደ አሰራርና ዝርፊያ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወደ ምድረ በዳነት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚሸጋገር ርግጠኞች መሆናቸውን፣ የአካባቢው ሰዎች ከመግለጻቸውም ባሻገር አስቸኳይ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ አካባቢው በሙሉ ወደ ምድረበዳነት ሊለወጥ ይችላል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ አግባብ በሌለውና በቂ ጥናት ባልተካሄደበት ሁኔታ የሚካሄደው የማእድን ማውጣት ስራ በአካባቢው ነዋሪዎች ጤና ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑም የኢሳት ዘጋቢዎች ገልጸዋል:: የአካባቢው ነዋሪዎች ታላላቅ ቋጥኞችን ለማፍረስ ተብሎ በሚደርሰው ፍንዳታ በሚነሳው አቧራ ለሳንባ እና ለመተንፈሻ አካል በሽታዎች እየተዳረጉ ነው።

ከሁሉም በላይ የአካባቢው ስነምዳር ቅርጽ እየተቀየረ መምጣት ተደጋጋሚ የመሬት መደርመስና የአለት ናዳ እያስከተለ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

ወርኪድስ ኢትዮጵያ ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ለሳሊኒ ኩባንያ አሸዋና ድንጋይ የሚያቀርብ እጅግ ግዙፍ የሆነ ኩባንያ ነው። ኩባንያው እጅግ ዘመናዊ መሳሪያዎችን በአባይ ሸለቆ ላይ አሰማርቶ የማዕድን ማውጣት ስራ እየሰራ መሆኑን በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወሳል።

## ግዜ

## ጥገኝነት የተከለከሉ በኖርዌይ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች የ600 ኪሎ ሜትር የተቃውሞ ጉዞ በኖርዌይ ጀመሩ

በዘረኛውና አምባገነን የወያኔ አገዛዝ በደል ሃገራቸውን ጥለው ለስደት የተዳረጉ በኖርዎይ ሃገር የሚገኙ ከ 35 በላይ የሚሆኑ ጥገኝነት ጠያቂ ኢትዮጵያዊያን ያቀረቡት ጥያቄ በኖርዎይ መንግስት ተቀባይነት በማጣቱ ተደጋጋሚ ጥረቶችን ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም ጥረታቸው እስካሁን ድረስ ባለመሳካቱ የኖርዎይ መንግስትን በመቃወም የ 627 ኪሎሜትር የ እግር ጉዞ መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከኦስሎ ኖርዎይ ባስተላለፈልን ዘጋባ ገለጸ::

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት የእግር ጉዞ የጀመሩት ኢትዮጵያዊያን ቀደም ብለው በኖርዎይ መንግስት ተቀባይነትን ለማግኘት የተለያዩ ሙከራዎችን ማድረጋቸው ከነኝህም ውስጥ በኦስሎ ከተማ የሰላማዊ ሰልፍ፣ በመቀጠልም በኦስሎ ከተማ በሚገኝ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመጠለል የርሃብ አድማ አድርገው እንደነበር አውስቱአል፤፤ ይሁን እንጂ የኖርዎይ መንግስት የኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን ጥያቄ ወደ ጎን በመተውና ውሳኔ እስኪታገኙ ጠብቁ በማለት በመሸጋገሪያ ካምፕ ውስጥ እንዲቆዩ ያደረገ ሲሆን፣ በመሸጋገሪያ ጣቢያ ውስጥ ሆነው ውሳኔ እየተጠባበቁ በነበረበት ወቅት ከካምፑ ባልታሰበ ሰአት በምሽት በፖሊስ እንዲባረሩ እንደተደረጉ ታውቁአል:: ስደተኞቹ በፖሊስ ከተባረሩባቸው ቦታዎች እንደገና በመሰባሰብና የመጠለያ ድንኳዋን በመትከል፣ ህይወታቸውን ለማቆየት ጥረት ያደረጉ ቢሆንም የኖርዎይ ፖሊሶች ድንኳኣናቸውን በማፈራረስ ኢሰብአዊ ድርጊት ፈጽመውባቸው እንደነበርም ታውቁአል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ነዋሪዎች "በክልላችን ረሀብ ገብቷል ብላችሁ አትናገሩ" ተብለው መታዘዛቸው ተዘገበ

"በክልላችን ረሀብ ገብቷል ብላችሁ አትናገሩ" ተብለው መታዘዛቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ነዋሪዎች ለኢሳት የምርመራ ቡድን መናገራቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ:: ኢሳት በዚሁ ዘገባው ላይ እንደገለጸው ወኪሎቹ ሰሞኑን በደቡብና በኦሮሚያ ክልል የገጠር አካባቢዎች በመዟዝ የአካባቢውን ህዝብ ያነጋገሩ ሲሆን፣ ከህዝቡ በተገኘው መረጃ መሰረት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ እርዳታ እንደሚከለክል፣ የህዝቡን መብት እንደሚያፍንና፣ ለኢንቨስትመንት በሚል ህዝቡን እንደሚያፈናቅል ከነዋሪው ለማረጋገጥ መቻላቸው ታውቋል።

ኢሳት በተጨማሪም አያይዞ እንደዘገበው በኦሮሞያ ክልል የሚገኙ አንዳንድ ነዋሪዎች፡ በፖለቲካ አቋማቸው የተነሳ የእርዳታ እህል እንዳያገኙ መከልከላቸውንም ኢሳት ዘጋቢዎቹ ያነጋገሯቸውን ነዋሪዎች ዋቢ በማድረግ አጋልጧል። በደቡብ ክልል ደግሞ ዘረኛው አገዛዝ በአካባቢው ረሀብ መግባቱን ለማንም እንዳትናገሩ ብሎ ለህዝቡ ትእዛዝ መስጠቱን በጋሞጎፋ ዞን የሚገኙ ነዋሪዎች ከኢሳት ዘጋቢ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ተናግረዋል።

ቀደም ብሎ በዚሁ የደቡብ ክልል ሰፋፊ ለም መሬቶች ለኢንቨስተሮች በርካሽ ዋጋ ሲቸበቸብ እነደቆየ በስፋት የተዘገበ ሲሆን ለዘመናት ከኖሩበት ቀየ እየተፈናቀሉ መሬታቸው ለኢንቨስተሮች እየተሰጠ መሆኑ እንዳሳዘናቸውም ለነዚሁ የኢሳት ዘጋቢዎች የአካባቢው ነዋሪዎች ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲዎቹን ዕርስ በርሳቸው ማጣረሱን ቀጥሏል፣ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ የግል የጤና ኮሌጆች አዳዲስ ተማሪዎች እንዳይመዘግቡ ትእዛዝ ማስተላለፉ ተሰማ

የግል ትምህርት ተቋማት እንዲስፋፉ ሌት ከቀን እየሰራሁ ነው በማለት ሲመጻደቅ የነበረው የወያኔ አገዛዝ ፣ ከሚቀለው ዓመት ጀምሮ የግል የጤና ኮሌጆች አዳዲስ ተማሪዎች እንዳይመዘግቡ ትእዛዝ ማስተላለፉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ ገለጸ። የግል ትምህርት ተቋማት ባለቤቶችም ይህን የዘረኛውን ወያኔ አዲስ ትእዛዝ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲዎቹን ዕርስ በርሳቸው እያጣረሳቸው ለመሆኑ መረጃ ነው በማለት ተናገሩ።

የዘረኛው አገዛዝ የውስጥ ምንጮች ለዘጋቢያችን እንደገለጹት ይህ በቅርቡ በይፋ ለህዝብ ይገለጻል የተባለው አዋጅ ከዚህ በኋላ የግል ተቋማት በጤና ትምህርት መሰማራት እንደማይችሉ የሚገልጽ ሲሆን፣ ከሚቀጥለው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ እንቅስቃሴ መጀመሩ ታውቋል። ይህ አዲስ መመሪያ ተግባራዊ ከተደረገ በጤናው ዘርፍ ተማሪዎችን ተቀብለው የሚያሰለጥኑ የግል ኮሌጆች በሙሉ እንዲዘጉ እንደሚያደርጋቸው ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የአንድ የግል ጤና ተቋም መምህር ለዘጋቢያችን እንደተናገሩት አገዛዙ ኮሌጆቹ የመዘገቧቸውንና በስልጠና ላይ የሚገኙትን ብቻ እንዲያስመርቁና ፡ አዲስ ምዝገባ ግን እንዳያካሂዱ ማስጠንቀቁ ታውቋል።

ቀደም ብሎ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተመሳሳይ መልኩ፡ የህግ ትምህርት የሚሰጡ የግል ኮሎጆች ስልጠናውን መስጠት እንዲያቆሙ አግዶ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ በሁዋላ ላይ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ለታሪክ አነባበብ ልዮነት - ሆደ ሰፊነትና አርቆ አሳቢነት!!

በኢትዮጵያዊያን መካከል የታሪክ አነባበብ ልዩነት አለ። ይህ ልዩነት ደግሞ ለበርካታ ችግሮቻችን መነሻ ሆኖ ቆይቷል። በተለይም ይህ የታሪክ አነባብ ልዩነት በሃገራች አንድነት ላይ የደቀነብን ፈተና ቀላል አይደለም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የታሪክ አነባበብ ልዩነት በሃገራች አንድነት ላይ የደቀነብንን ፈተና መወጣት የኛ - ማለትም የዚህ ዘመን ትውልድ - ኃላፊነት ነው ብሎ ያምናል። በዚህ እምነቱ መነሻም በ2010 እ.አ.አ. ባሳተመው “ነፃነት፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲና አንድነት” በተሰኘው መጽሃፉ ውስጥ ስለአገር አንድነት በአጠቃላይ፤ በተለይ ደግሞ ስለታሪክ አነባበብ ልዩነት፤ ይህ ልዩነት የሃገራችንን አንድነት አደጋ ላይ መጣሉን እና መፍትሄውም ምን እንደሆነ ሰፋ ያለ ትንተና አቅርቧል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ያልተቋጩ በመሆናቸው ከላይ በተጠቀሰው ጽሁፍ ላይ የሰፈሩትን ዋና ዋና ሃሳቦችን እንደገና ማስታወስ አስፈልጓል።

የአንድነት ጥያቄ በሃገራችን የፖለቲካ መድረክ ወሳኝነት ካላቸው ከዋነኞቹ አወዛጋቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። እንዲያውም የጉዳዩን አሳሳቢነት ከፍ ከሚያደርጉ ምክንያቶች በፖለቲካ ኃይላቱ መካከል ጽንፍ የደረሰ የሚመስል ከቃላት አጠቃቀም ጀምሮ ያለ የታሪክ አተረጓጎም ልዮነት መኖሩ ነው።

በአንድ በኩል የሃገሪቱን ታሪክ ገናናነት፣ ታላቅነት እና ቀድሞ የነበራትን ግዛቶች በማስታወስ የሚቆጨው ክፍል፣ የአሁኗ ኢትዮጵያም የአንድነት መሠረት ከጥንት አክሱማዊ ስልጣኔ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ተጋድሎና ፍልሚያ የተጠበቀ እንደሆነ ይተርካል። የተካሄዱት የመስፋፋት ዘመቻዎች ታሪካዊ መሠረት ያላቸውና ሃገሪቷን አንድ ለማድረግ የተደረጉ ሲሆን፤ ይህ አይነቱ ጥረት ኢትዮጵያን የተለየች ሃገር እንደማያደርጋት፤ አብዛኞቹ የዓለም ሃገራት ያለፉበት መንገድ እንደሆነ በመጥቀስ ይከራከራል።

በሌላ በኩል የምናገኘው የታሪክ እይታ፣ ሃገሪቱን አንድ ለማድረግ የተደረጉ ዘመቻዎችና ጥረቶች በኃይል የተሞሉና ቀድሞ ራስ-ገዝ የነበሩ ክልሎችና ግዛቶችን ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት በማዳከም ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይናገራል። ይህ እይታ በሃገር ግንባታው ሂደት በተከሰቱት ችግሮች ላይ በማተኮር የሃገሪቱ አንድነት በሃይልና በጭቆና ላይ ስለተመሰረተ እና ቀድሞ የነበሩትን ራስ-ገዝ ግዛቶችን በማጥፋቱ መፍትሄው እስከ መገንጠል ሊደርስ የሚችል የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ተግባራዊ ማድረግ ነው በማለት ይሟገታል።

ከእነዚህ ሁለት ጽንፎች በተለየ የመካከለኛውን ስፍራ ይዞ የሚገኘው እይታ የሃገሪቱን አንድነትና የፖለቲካ ችግር መፍትሄ ማስገኘት የሚቻለው ታሪክን እንዳለ በመካድ ወይንም እንዳለ ተቀብሎ በማጋነን ሳይሆን ካለፈው ጥሩ ያልሆነ አጋጣሚ ትምህርት በመቅሰም፤ ከቂም በቀል በመራቅ፤ ስህተቶች እንዳይደገሙና ፈተና ውስጥ እየወደቀ ያለውን አንድነታችንን በዴሞክራሲያዊ መሰረት ላይ በመገንባት ነው የሚል ነው።

ግንቦት 7 የሶስተኛው የታሪክ እይታ አራማጅ ነው። አሁን የገጠመን የአገር አንድነት ችግር መንስኤ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የአገዛዝ ሥርዓቶቹ በነበራቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊና አምባገነናዊ ባህሪ ምክንያት የእኩልነት መፍትሄ መስጠት አለመቻላቸው ነው ብሎ ያምናል። አንዳንዶቹ ቀደም ያሉ ሥርዓቶች በነበሩበት የታሪክ ማእቀፍ ለምን የዴሞክራሲንና የእኩልነትን መርህ የአገዛዛቸው መሠረት አላደረጉም ተብለው ሊወቀሱ የሚችሉ ባይሆኑም፣ ለዘመናችን ጠጋ ያሉት ከአጼ ኃይለስላሴ አገዛዝ ጀምሮ የነበሩት የአገዛዝ ሥርዓቶች አንዱ ከሌላው በባሰ ለሃገር አንድነት አደገኛ የሆነውን ኢ-ዴሞክራሲያዊና አምባገነናዊ አገዛዛቸውን አጠናክረው መቀጠላቸው ተጠያቂ ያደረጋቸዋል። በተለይ ደግሞ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የአገዛዝ ሥርዓት ዴሞክራሲና እኩልነት የዓለምና የአገራችን ህዝብ ቋንቋ በሆነበት ዘመን ስልጣን ላይ የተፈናጠጠ በመሆኑ በዘር ላይ ለተመሰረተ መድሎው፣ አፈናና ጭቆናው አለማወቅን ምክንያት አድርጎ ሰበብ መስጠት የማይችል ብቻ ሳይሆን በሚተገብረው ዘረኛ የእብሪትና የዘረፋ ፖሊሲ በአገር አንድነት ጉዳይ ላይ የጋረጠበን ፈተና ከቀድሞዎቹ ዘመናት የባሰ ሆኗል።

በግንቦት 7 እምነት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት ሳንጥል በአንድነታችን ላይ የተደቀነውን ችግር መፍታት አንችልም። በብዙ የዓለማችን ሃገሮች ታሪክ እንደታየው የአገር ግንባታ ሂደት በአመጽ በእሳትና በብረት፤ በወረራና በመስፋፋት የተጀመረ ሂደት ነው። በዛው ልክ ደግሞ በእንዲህ ዓይነቱ የአመጽ መሳሪያነት የተጀመረን አገርን አንድ የማድረግ ሂደት፣ በዜጎች መካከል ወደተፈጠረ መሠረቱ የጠበቀ የአገር አንድነት መቀየር የተቻለው የህግ የበላይነት፣ የእኩልነትና የዴሞክራሲ መብቶች ለዜጎች በሙሉ ለማጎናጸፍ በተደረገ ጥረት፤ በእነዚህ መብቶች ላይ የተገነባ ለዜጎች በሙሉ የስልጣኔና የብልጽግና ትሩፋት ማዳረስ የሚችል ሃገር በመገንባት ነው። ግንቦት 7 “ዲሞክራሲ ሂደት እንደሆነ ሁሉ አንድነትም ሂደት ነው” የሚለው ለዚህ ነው። ከፋብሪካ እንደሚወጣ እቃ አንድነቱን ጨረሶ የተወለደ አገር በታሪክ አይታወቅም። የዜጎችንና የቡድኖችን መብቶች በእኩልነት የማክበሩ ሂደት በቀጠለ መጠን፤ ዲሞክራሲ በተግባር በስራ ላይ በዋለ መጠን፣ ድህነትና መሃይምነት ሲቀንሱ የአገር አንድነት ፈተናዎች እየቀነሱ እንደሚሄዱ ግልጽ ነው።

ግንቦት7 የአንድነታችን ጽኑ መሠረት መቆም የሚችለው አሁን በጫንቃች ላይ ያለውን ዘረኛና አፋኝ የአገዛዝ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ መሠረት ባለው ህዝባዊ ሥርዓት መተካት ከቻልን ብቻ ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም በሃገር ግንባታው ሂደት የተከሰቱ አስከፊ ሆነ በጎ ኩነቶችን ወደጎን ሳይገፉ እንደ ትምህርት በመውሰድ በፍትህ፣ በእኩልነትና ዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ በመቆም ልዮነትን ተቀብሎ ለአንድነት መስራት ያስፈልጋል የሚል ጽኑ እምነት አለው።

በግንቦት 7 እምነት፣ ቀደም ባሉት እና አሁን በጉልበት ሥልጣን ላይ ባለው ሥርዓቶች ኢ-ዴሞክራሲያዊነት ባስከተለው ኋላቀርነት ምክንያት ሰፊ የሆነ አገራዊ አንድነት አልተፈጠረም። የነገዋ ኢትዮጵያን አብረን እንኑርባት የምንል ከሆነ ዛሬ የቻልነውን ያህል ለሁላችንም እንድትስማማን አድርገን ማሟላት መብታችን፣ ግዴታችን እና ጥቅማችንም ነው። በቀደምቶቻችን የተመሰረተው በግዛት ላይ የተመሠረተ አንድነት ዴሞክራሲያዊ መሠረት እንዲኖረው በማድረግ ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች የባለቤትነትና የእኩልነት ስሜት እንዲፈጠርባቸው ማድረግ የኢትዮጵያ ዘላቂ አንድነት የሚያሳስበን ወገኖች ሁሉ የጋራ ሥራ ነው ብሎ ግንቦት 7 ከልቡ ያምናል።

የትላንትናዋን ሳይሆን የነገዋ በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሰረተችውን ዲሞክራሲያዊትና ሉዓላዊት ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ በሆደሰፊነትንና በአስተዋይነት ሁላችንም ተባብረን እንድንቀሳቀስ ግንቦት 7 ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በአገራችን ተደጋግሞ የሚከሰተው ረሃብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ባለፉት 60 አመታት ጊዜ ውስጥ ታይቶ በማይታወቀውና የምስራቅ አፍሪካ ሃገራትን ዜጎች እንደቅጠል እያረገፈ ባለው ረሃብ ከ12.5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ተጎጂ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ከነኝህ ረሃብተኞች ውስጥ ከ4.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ በስፋት ሲዘገብ የቆየ መሆኑ ይታወሳል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በጉልበት እየገዛት ባለቺው ኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄዶ እጂግ አስከፊ ከሆነ ደረጃ ላይ መደረሱ በስፋት እየተዘገበ ባለበት ባሁኑ ወቀት ዘረኛው አገዛዝ አሁንም በሃገሪቱ ፈጣን የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት እየተመዘገበ ነው በማለት በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የመገናኛ ብዙሃን ህዝብን ሲያደነቁር እንደሚገኝ በስፋት መግለጻችን ይታወቃል። በኢትዮጵያ ባጠቃላይ በምግብ እህል ርዳታ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር ከ12 ሚሊዮን በላይ ሲሆን እስከዛሬ ድረስ ታይቶ የማይታወቅ የዋጋ ንረት መከሰቱንና የዋጋ ግሽበትም ከ40 በመቶ በላይ ማለፉን የተለያዩ የዜና አውታሮችም መግለጻቸው ይታወሳል።

## በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ነዋሪዎች "በክልላችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላም በኩል የኢሳት ዘጋቢዎች የብሪቲሽ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ ቢቢሲ የእርዳታ እህል ለተገቢው አላማ እንዳይውል ተደርጓል፣ ከምእራባዊያን ለወያኔ አገዛዝ የሚጎርፈው በቢሊየን የሚቆጠር የዶላር ርዳታም ህዝብን ለማፈንና ተቃዋሚ ፓርቲዎችንም ለመጨፍለቅ ውሏል በማለት በቅርቡ የሰራው የምርመራ ዘገባ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ መቻላቸውን የኢሳት ዘጋቢዎች የላኩት ሪፖርት ማመልከቱ ታውቋል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛ ቁንጮዎች ቢቢሲ ያወጣው ዘገባ እጅግ በጣም ያበሳጫቸው መሆኑንና የቢቢሲንም ዘገባ የማዳፈን እንዲሁም በቢቢሲ ላይ የስም ማጥፋት

## ጥገኝነት የተከለከሉ በኖርዎይ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ ሁሉ የበደል መደራረብ ያስመረራቸው እነኝህ ስደተኞች በመጨረሻ ለኖርዎይ ህዝብ ችግራቸውን ለማስረዳት ከኦስሎ ከተማ ትሮንዳሄም እስከሚባለው ሌላ ከተማ ድረስ የስድስት መቶ ሃያ ሰባት ኪሎሜትር የእግር ጉዞ መጀመራቸውን የነኝሁ ስደተኞች አባል የሆነ ወጣት ለዘጋቢያችን ገልጹአል።

ከኦስሎ ዘጋቢያችን ጋር ውይይት ያደረገው ይሄው ወጣት እንደተናገረው ይህ የእግር ጉዞ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ የሚገኙ ኢራናዊያንንም ያካተተ ሲሆን ጉዞው ሊጀመር ታቅዶ የነበረ ባለፈው ሃምሌ 23 ቀን 2003 ዓም ቢሆንም ኦስሎ ከተማ ደርሶ በነበረው ፍንዳታ ምክንያት መዘግየቱን ተናግሩአል።

ዘጋቢያችን በመላው አለም ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የሚያስተላልፈው መልእክት ካለው እድሉን እንዲጠቀም የጠየቀው ወጣት እንደተናገረው ለእኛ እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያዊያን በየበረሃውና በየሃገሩ እያለቁ ላሉት ንጹሃን ዜህጎች ተጠያቂው ዘረኛውና ፋሽስቱና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነው፣ በመሆኑም ድምጻችንን፣ ሃሳባችንን፣ ጉልበታችንን.፣ አንድ በማድረግ፣ ይህን ዘረኛ አገዛዝ መዋጋት ካልቻልን፣ የህዝባችን የስደት መከራ አያበቃም። በመሆኑም በመላው አለም ተበትናችሁ ለምትገኙ የተለያየ የፖለቲካ ድርጂቶች ሁሉ፣ አቁአማቺሁንና፣ ልዩነታችሁን ወደ ጎን በመተው በየሰው አገሩ መንገድ ላይ ለምንተኛ ለኛ ኢትዮጵያዊያን ስትሉ፣ አንድ ሆናችሁ ይህንን አረመኔ አገዛዝ ከምድራችን እንድናባርር ጥሪ እናቀርባለን ብሉአል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲዎቹን ዕርስ በርሳቸው ማጣረሱን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በደረሰብት ጫና ውሳኔውን መልሶ ለማንሳት መገደዱ ይታወሳል። በአሁኑ ጊዜ በግልም ሆነ በመንግስት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ከተመረቁ በሁዋላ በፍትሀዊ መንገድ ተወዳድረው ስራ ለማግኘት ባለመቻላቸው የድርጅት አባላት እንዲሆኑ እንደሚገደዱ ሂውማን ራይተስ ወችን የመሳሰሉት ድርጅቶች በተደጋጋሚ የዘገቡት ጉዳይ ነው።

የዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ አዲስ ርምጃ አስመልክቶ ለዘጋቢያችን አስተያየት የሰጡት መምህር እንደገለጹት ወያኔ የተለያዩ ውጥረቶችና ፈተናዎች ሲገጥሙት ሁሌም እንደሚያደርገው ምንም ያልታሰበበትና እቅድም የሌለበት ርምጃ ይወስዳል፣ ርምጃውን ከወሰደ በኋላ፣ ያስባል፣ የወሰደው ርምጃ ስህተት ሆኖ ሲያገኘው እንኳን ይቅርታ ጠይቆ ከማስተካከል ይልቅ ርምጃዬ ትክክል ነበር ብሎ ይከራከራል፣ እናም በጤናው ዘርፍ አሁን የወሰደው ርምጃም ተመሳሳይ እጣ ፈንታ እንደሚገጥመው ምንም ጥርጥር የለኝም በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## የግንቦት7 አላማ ምንነት፤ ለምንና እንዴት በሚል ርዕስ ከታተመው የግንቦት7 መጽሃፍ የተወሰደ ( ክፍል 1 )

### ሰው፣ እውቀትና ነጻነት

ነጻነት ከማናቸውም ነገር ቀድሞ ከራስ የማንነት ግንዛቤ ከሚመጣ እውቀት የሚመነጭ ነው፡፡ ይህ እውቀት ደግሞ የሰው ልጆች ብቻ ተፈጥሮ ነው፡፡ ለምሳሌ ፍጥረትን ተራ በተራ ብንወስድ፣ ድንጋይን የመሳሰሉ ህይወት የሌላቸው ግኡዛን ስለራሳቸው ምንም እውቀት እንደሌላቸው እንረዳለን፡፡ ብዙ ቋጥኞች በአንድ ላይ ተከማችተው በሚገኙበት ሁኔታ አንዱ ቋጥኝ ስሌላው አጠገቡ ስለሚገኝ ቋጥኝ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ አበቃ ድንጋይ ድንጋይ ነው፡፡ እጽዋትም፣ ፊታቸውን ጸሃይ ፍለጋ ወደ ጸሃይ መውጫና መጥለቂያ የሚያዞሩ ወይም ውሃ ፈለጋ ስራቸውን በመቶ ሜትሮች ከምድር በታች አስገብተው የሚያስሱ፣ ሲነኳቸው የሚሸማቀቁ ቢኖሩም በተፈጥሯቸው ከድንጋይ የሚለያቸው ነገር የለም፡፡ አንድ ዛፍ አጠገቡ ስላለው ዛፍ እውቀት የለውም፡፡ ወይም ከዛፉ እግር ስር ስለበቀለችው ጽጌረዳ ውበት አይደነቅም፡፡ ግንዱን ተደግፋ ስለምትታከከው ላም ወይም መጥረቢያውን ስሎ ሊገነድሰው ስለሚጠጋው ዛፍ ቆራጭ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ዛፍ ዛፍ ብቻ ነው። የተለየ ሌላ ተፈጥሮ ወይም ምንነት የለውም፡፡ ከዛፉ ስር ያቆምናት ላምም ከዛፉ የተሻለ ከባቢያዊ የደመነፍስ እውቀት ቢኖራትም፣ ተፈጥሮዋ ከዛፉ ብዙ ልዩነት የለውም፡፡ በማሽተትና በማጣጣም አካባቢዋን ማወቅ ብትችልም በማሽተትና በማጣጣም አቅሟ ላይ ማሰላሰልና መመራመር አትችልም፡፡ በአንድ ቃል ስለላምነቷ የምታውቀው ነገር የላትም፡፡ የራስ ግንዛቤ የሚባል ነገር የላትም፡፡ የሚቀልባት ባለቤቷ አንድ ቀን ሊያርዳት እንደሚችልና ህልውናዋም ሞት በሚባል ፍጻሜ እንደሚጠናቀቅ አታውቅም፡፡ ይህ ራስን የማወቅ፣ ራስን ከአካባቢ፣ ከእንስሳውና ከእጽዋቱ፣ ከቋጥኙና ከድንጋዩ ለይቶ እኔ የሚል የራስ ግንዛቤ ያለው ሰው ብቻ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ብቻ ሳይሆን፣ ከጎኑ ካለው ሌላው ሰው ጭምር ራሱን የሚለይ፣ የራስ ማንነትና የተለየ የግለሰብነት ግንዛቤና ስሜት ያለው ልዩ ፍጥረት ነው፡፡

አንዳንድ ሃይማኖቶች ይህ የሰው ልጅ የራስ እውቀት ከፈጣሪው ያገኘው ልዩ ተፈጥሮ ነው ይላሉ። ይህንንም ሲያስረዱ የሰው ልጅ፣ ከሌሎች ፍጥረታት ብቻ ሳይሆን ከጎኑ ካለው ሌላው ሰው ጭምር ራሱን የሚለይ፣ የራስ ማንነትና የተለየ የግለሰብነት ግንዛቤና ስሜት ያገኘው ፈጣሪው ልዩ አድርጎ ስለፈጠረው መሆኑን ይስማማሉ፡፡ ከእምነት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው የተለያዩ ፍልስፍናዎችም ሰውን ልዩ የሚያደርገው ተፈጥሮው ወይም ባህርይው ይህ ማንነቱን በራሱ ለይቶ ለማወቅ ያለው ነጻነት መሆኑን ይስማማሉ፡፡

ቀደም ብለን እንደ ጠቀስነው ድንጋይ በድንጋይነቱ ከታሰረበት የድንጋይነት ማንነቱ ራሱን ነጻ ማድረግ የማይችል በመሆኑ በድንጋይነት ለዘልአለም ይቀጥላል፡፡ እጽዋትና እንስሳትም እንደዚሁ፡፡ ሰው ግን በአንድ በኩል በተሰራበት ንጥረ ነገር፣ በስጋነቱና በፈራሽነቱ፣ ከድንጋዩ ከጽዋቱ ከእንስሳው የማይለይ ቢሆንም፣ እንዲህ አይነቱን አካለዊ ሰውነቱን ጨምሮ ስለማንነቱ የራስ ገንዛቤ አለው፡፡ «እኔ፣ እኔ ነኝ አንተም እርስዋም አይደለሁም፡፡ ያ ጠረጴዛም ወይም ብርጭቆ አይደለሁም» የሚል ደመነፍሳዊ ያልሆነ ግንዛቤ አለው፡፡ ሰው እራሱን ካገኘበት የተፈጥሮ ትርምስ ራሱን መንጥቆ ማውጣት የሚችል ተፈጥሯዊ ነጻነት ባይኖረው፣ ራሱን ከአካባቢው ለይቶ የእኔነት ግንዛቤ ሊኖረው አይችልም ነበር፡፡ ከፍጥረት ጋር አንድ ሆኖ የፍጥረትን ረቂቅነት፣ ቀለምና ቅርጽን መለየት የማይችል ከየትኛውም ፍጥረት ልዩነት የሌለው የተፈጥሮ አካል ሆኖ ይቀበር ነበር፡፡ ሰው እንደ ድንጋዩ፣ ዛፉና ላሟ እራሱን ከተሰራበት አካላዊ ተፈጥሮ ነጻ ማድረግ ባይችል ኖሮ እነሱኑ ሆኖ ይቀር ነበር፡፡

የሰው ልጅ ነጻነቱ አካላዊ ካልሆነው ሌላው የሰው ልጅ ተሰጥኦ ከህሊናው ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው፡፡ የሰው ልጅ ህሊናን ከነጻነት ለይተን ማሰብ አንችልም፡፡ ይህ ማለት ነጻነትና ሰውነት በማይበጣጠሱ ክሮች የተተበተቡ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ የራስ እውቀት ጅማሮ ግን ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን አስቀድሞ የሰው ልጅ በተላበሰው ነጻነት ራሱን ማወቅ በመቻሉ የመጣ ነው፡፡ ነጻነት ሰው ከሆንን በኋላ የሚሰጠን ወይም የምንላበሰው ባህርያችን ሳይሆን የሰውነት መለያችን ነው፡፡ ሰው መሆናችንን ማወቂው ብቸኛው ነገር ነጻነት ነው፡፡ ይህ እውቀት፣ ይህ ነጻነት የሰው ልጆችን ከአንስሳት የተለዩ ልዩ ፍጥረቶች ለመሆናቸው ማስረጃ በመሆን ሲያኩራራቸው ይታያል፡፡ ይህ እውቀትና ነጻነት ግን የሚያኩራራና የሚያስደስት ብቻ ሳይሆን በግልባጩም ለሰው ልጅ እዳና እርግማን በመሆን የከፍተኛ ሃዘን መከራና ጣር ምንጭ ጭምር ነው፡፡

### የነጻነት እርግማን፣ የእውቀት እርግማን

የተለያዩ እምነቶች «የሰው ልጅ ስለራሱና ስለአካባቢው ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት አለው። ፍላጎቱ ጠንካራ በመሆኑም በራሱ ፍላጎትም ሆነ፤ በሰይጣን እየተገፋ ፈጣሪው አታድርግ ያለውን ከማድረግ አልተመለሰም። የድርጊቱን ውጤት ለማወቅ ስለሚጓጓ፤ ፍላጎቱን ከማሳካት የሚያግደው አንዳችም ሃይል የለም። ነጻ ተፈጥሮው የፈጣሪውን ትዕዛዝ እንኳ እስከመጣስ ያደርሰዋል። በዚህም ምክንያት የሰራው ሁሉ እየተባረከለት ከሚኖርባት፣ ረሃብ፣ ችጋርና በሽታ የሚባል ነገር ከማይታወቅበት፣ ፍጥረታት ሁሉ ለጥቅሙ ብቻ ከተፈጠሩባት ገነት/ጄኔት ከተባለ ስፍራ ወደ አደገኛይቱና በውስጧም ያሉ ፍጥረታት ሁሉ በጥረቱ ካላሸነፋቸው በስተቀር ሊጎዱት ወደሚችሉባት ምድር መጣሉን ይነግሩናል፡፡ «ሰው ራሱን አወቀ፣ እርቃኑን መሆኑን ተረዳ። ሟችና ፈራሽ መሆኑን ተገነዘበ። ያለማንም ድጋፍ በራሱ ድካምና ጥረት ማስኖ የሚኖር ለራሱ እንዲወስን በውሳኔውም ወደ ጽድቅና ኩነኔ ወደ ገነት/ጄኔትና ገሃነም የሚጓዝ ፍጥረት መሆኑን ተገነዘበ፡፡ ሆኖም ፈጣሪው ሰውን ከገነት/ጄኔት አውጥቶ ወደ ምድር ሲወረውረው፣ያሻውን ማድረግና መፍጠር እንዲችል ካደረገው ከነጻነቱ ጭምር ጋር ነው፡፡ ይህንን ነጻነቱን በመጠቀም በሚሰራው ግን ይጠየቅበታል» ይላሉ፡፡

የተለያዩ ፍልስፍናዎችም ሰው በራሱ ምርጫና ውሳኔ ኖሮ የሚሞት ፍጥረት መሆኑን ያስረዱናል፡፡ ነጻ ፍጥረት በመሆኑ ጥሩና መጥፎውን የሚለየው በራሱ ነጻ ጥረት እንጂ አስቀድሞ ከተደነገገበትና ማምለጫ በሌለው አሳሪ ህግ አለመሆኑን ያብራራሉ፡፡ የሰው ልጅ ለሚፈጽመው ድርጊት በሙሉ ከራሱ ውጭ ሌላ የሚጠየቅ ሃይል የለም፡፡ ሰው እንደ ድንጋይ እንደዛፍና እንስሳ አስቀድሞ በተወሰነ ባህርይ የታሰረ አይደለም፡፡

ሰው በርጩማ አይደለም። በርጩማ ለመቀመጫነት ታስቦ የተሰራ ነው። ሰው እንደ በርጩማ ምን አገልግሎት እንደሚኖረው አስቀድሞ ታስቦ፤ የተጠረበ አይደለም፡፡ ሰው ምን መሆን እንደሚገባው በህይወት መንገድ ላይ የሚገጥሙትን ፈተናዎች ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት እየወሰነ፣ በነጻነቱ በሚወስነው ውሳኔ እራሱን ደግሞና ደጋግሞ እንደአዲስ እየፈጠረ የሚኖር ፍጥረት ነው፡፡

ሰው እንደሙቀጫ ወይም ዘነዘና ምን መሆን እንደሚገባውና ለምን መገልገያነት እንደተፈጠረ አስቀድሞ አልተደነገገም፡፡ የሰው ልጅ ያለቀለት የምንነቱ መገለጫ ይዞ ያልመጣ መሆኑን የሚስረዱን የፍልስፍና ዘርፎች እንደሚሉት ከሰው ባህርይ የማይቀየር ያለቀለት ሆኖ ከሰው ጋር የሚመጣ ነገር ቢኖር ነጻነቱ ብቻ ነው፡፡ አንድ ሰው መምህር፣ መለዮለባሽ፣ ማጅራትመቺ፣ በጎአድራጊ፣ የመሆን እጣውን በህይወቱ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ሊቀይራቸው ይቻለዋል። በሰውነቱ ይዞት የመጣውን የራስ ግንዛቤና ነጻነቱን ግን እንዳሻው ሊቀይረው አይችልም፡፡ ነጻነት ማለት ሰውነት፣ ሰውነት ማለት ነጻነት ነው፡፡ ሰውን ከነጻነቱ ውጭ ማሰብ አይቻልም፡፡ ያለነፃነት ሰው የሚባለውን ፍጡር ማሰብ አይቻልም። "ነጻነት ለሰው ልጅ የማይመለጥ እጣ፤ የማይመለጥ እርግማን ነው" የሚባለውም ለእዚህ ነው፡፡

### ነጻነትና ሞት፤ የነጻነት ፍራቻ

የሰው ልጅ የፍጥረቱ ባህርይ ነጻነትን የተላበሰ መሆኑን አትተናል፡፡ ሌላው ሰውን ልዩ የሚደርገው ነገር አስቀድሞ የራሱን መጨረሻ ማየትና በፍጻሜው ላይ ማሰላሰል የሚችል ፍጥረት መሆኑ ነው፡፡ አስቀድሞ ሟች መሆኑን አውቆ የሟችነትን የማይመለጥ እጣና እርግማን ተሸክሞ ይኖራል፡፡ ብዙዎቻችን ስለነጻነት ካለን ቀና አመለካከት በመነሳት የሰው ልጅ ከነጻነት ጋር እንዲህ በጥብቅ መተሳሰሩ ታላቅ ጸጋ ነው እንል ይሆናል፡፡ ይሁንና የነጻነት ጉዳይ በተለምዶ ከምናውቀው የሃገር ነጻነት፣ የመናገርና የመጻፍ ነጻነት ባሻገር ብዙ መዘዞችን ተሸክሞ የሚመጣ መሆኑን ስንረዳ ብዙዎቻችን ስለነጻነት ጸጋ መሆን ያለን አመለካከት ይቀየራል፡፡ ነጻነት የሚያማልሉ ገጽታዎች ያሉትን ያህል እንደሬት የሚመሩ ገጽታዎችም ያሉት ነው።

ነጻነት በህይወታችን ለምንወስዳቸው ማናቸውም ውሳኔዎች መሰረት ነው፡፡ ነጻነት በምንለብሰው ልብስና በምንመገበው የምግብ አይነት በሚደረግ ምርጫ የሚገለጽ የውሳኔ ነጻነት ብቻ ቢሆን ብዙ ባላስጨነቀን ነበር፡፡ የሰው ልጅ ግን ተራ በሆኑ ፍለጎቶቹ ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በህይወቱ ላይ ከፍተኛ መዘዝ የሚስከትሉ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን እንዲወስን ይገደዳል፡፡ ሰው ማለቂያ አልባ ውሳኔዎችን እየወሰነ የውሳኔዎቹ መዘዝ በጎም ይሁኑ መጥፎ ተቀብሎ የሚኖር ፍጥረት ነው፡፡

ሰው በአንድ በኩል በማናቸውም ጉዳይ ላይ የመወሰን ነጻነት እንዳለው ያውቃል፡፡ ይህ ውሳኔ ጠንከር ያለ መዘዝ ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ የበለጠ ይሸበራል፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በሥራው ቦታ ጠባይ፣ በአለቃው ጠባይ፣ በሚሰራው ሥራ ዓይነት፣ የማይወደውን ሥራ ለአመታት ሲሰራ ቆይቶ "አሁንስ በቃኝ" ለማለት ሲነሳ በጭንቅላቱ ብዙ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ "ይህን ሥራ አቁሜ ምን እሆናለሁ?" ይላል፤ ሌላ የሚስደስተው ሥራ በቀላሉ የሚያገኝ ከሆነ ግን ችግር አይኖረውም፡፡ ነገር ግን ምንም ሥራ የማያገኝ ከሆነ የውሳኔው መዘዝ ግልጽ ይሆናል፡፡ «ይህንን ሥራ አቁሜ ምን እበላለሁ? የቤት ኪራይስ ምን እከፍላለሁ?» ወዘተ ማለት ይጀምራል፡፡ ልጆችና ቤተሰብ ካለው ደግሞ ችግሩ የበለጠ ይወሳሰባል። በሥራው በጣም የተንገፈገፈ ከሆነ "ከእዚህ ሥራ ለምን ተርቤ አልሞትም? ለምንስ በረንዳ አላድርም?" የሚሉ አማራጮች በጭንቅላቱ መመላለስ ይጀምራሉ፡፡

የሰው ልጅ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት በተላበሰው ፍጹማዊ ነጻነቱና ውሳኔውን ተከትሎ በሚመጣው መዘዝ መሃል ተወጥሮ የሚኖር ፍጥረት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከላይ ከጠቀስነው ምሳሌ እጅግ አስከፊ መዘዞች ያሉትን ውሳኔዎች የሚወስንበት ሁኔታዎች በህይወቱ ያጋጥመዋል፡፡

በአለም መገናኛ ብዙሃን ሁሌም ተደጋግሞ የሚታየው በቻይናው ታይናማን አልቂት ጊዜ ታንክ ፊት ቆሞ ታንኩን አላሳልፍም ያለው ወጣት ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ታንኩ ፊት የመቆምና ያለመቆም ውሳኔ የመኖርና ያለመኖር ውሳኔ ነው፡፡ ከታንኩ ፊት እቆማለሁ ብሎ መወሰን ከሞት ጋር ፊት ለፊት መፋጠጥን ያስከትላል፡፡ ይህ ሁኔታ እንደዚህ ዓይነቱን አስፈሪ ውሳኔ የመወሰን ነጻነት የሰው ልጆች በሙሉ የተላበሱት መሆኑን ያሳየናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎቻችንም ከየትኛውም ታንክ ፊት መቆም እንደምንችል ይጠቁመናል፡፡ ከታንኩ ፊት መቆም ለአንድ ቻይናዊ ወጣት ብቻ የተሰጠ እንዳልሆነ ያመላክተናል፡፡ የሰው ልጅ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚፋጠጠው ስፋቱ ማለቂያ ከሌለው ነጻነቱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከገዛ ሞቱ ጋርም ይሆናል፡፡ ነጻነትና ሞት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው የሚባለውም ለእዚህ ነው፡፡ ነጻነቱ ገደብ የሌለውን ነገር ለመፈጸም የሚያስችለው መሆኑን ሲረዳ ይህም ማለት ሞት የሚስከትልበትን ድርጊት መፈጸምን የሚጨምር መሆኑን ሲያውቅ ሞቱን ብቻ ሳይሆን ነጻነቱንም ጭምር መፍራት ይጀምራል፡፡ ሞትን ስንሸሽ እንደምንኖር ሁሉ ነጻነታችንን ስንሸሽ የምንኖር ፍጥረቶች የሚያደርገን ይህ ሃቅ ነው፡፡

ይህ የነጻነት ፍራቻ ብዙዎቻችን ህሊናችን የማይቀበለውን ድርጊት እንድንፈጽምና የማንፈልገውን ህይወትና ኑሮ እንድንኖር የሚያደርገን ዋናው ምክንያት ነው፡፡ የውሳኔያችንን መዘዝ ለመቀበል ድፍረቱን ስናጣ፣ በሰውነታችን የተላበስነው፣ ሁኔታዎችን የመቀየርና እምቢ የማለት ነጻነት ያለን ፍጥረት መሆናችንን መካድ የተለመደ ነው፡፡ ያለንበትን ሁኔታ ለመቀየር ምርጫ የሌለን አድርገን እራሳችንን ማየት እንጀምራለን፡፡ ነጻነትን የመሰለ ሰውን ከምንም ነገር የሚለየውን ባህርይ መላበሳችንን እንክዳለን፡፡ ለራሳችን እየዋሸን ምንም አይነት የሰብአዊነት ሞራል የሌለው ኑሮ እንኖራለን፡፡ ይህ ድርጊታችን እጅግ አስገራሚና ከራሳችን ጋር እንድንፋጠጥ በሚያደርጉ ዝንባሌዎች እንደሚገለጽ ቀጥሎ የምናየው ይሆናል፡፡ (ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## በአፍሪካ እየተካሄደ ያለው የመሬት ቅርምት የአገሩን ህዝብ ከመሬቱ በማፈናቀል በክፍለ-አህጉሩ የተከሰተውን ረሀብ ማባባሱ ተገለፀ

ተቀማጭነቱ ዋሽንግተን የሆነው ወርልድዎች ኢንስቲትዩት፤ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ሪፖርት በመካከለኛውና ከሳህራ በታች ባሉ በ25 የአፍሪካ አገራት የሚገኙ ገበሬዎችና የገጠር ነዋሪዎች፤ያለጥናት በተደረገ የመሬት መቀራመት ይዞታቸውን አጥተው ለከፋ ችግር ተጋልጠዋል አለ።

ወርልድ ዎች ኢንስቲትዩት እንደገለጸው በዚህ መልኩ እየተከሰተ ላለው ችግር በዋነኝነት ሳዑዲ አረቢያንና ቻይናን ጨምሮ የመካከለኛውና የሩቅ ምስራቅ አገራትን ኮንኗል።

በሌላም በኩል ጉዳዩን አስመልክቶ ሬውተርስ እንደዘገበው፤ መሬት መቀራመቱን በዘመቻ መልክ የተያያዙት እነዚህ አገሮች፤ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ2006 እስከ 2009 ባለው የሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ፤ ከ 15 እስከ 20 ሚሊየን ሄክታር የሚሆን መሬት መከራየታቸውን ጥናቱ ጠቁሟል።

“ወደ አፍሪካ በማቅናት ነዋሪዎችን እያፈናቀሉ በወደቀ ዋጋ መሬት እየተከራዩ ናቸው” ያላቸውን አገሮች ”ራስ ወዳዶች” በማለት የወቀሰው ወርልድ ዎች፤ መሬትን ለውጭ አገር ባለሀብቶች በርካሽ ዋጋ ለማከራየት- ተወላጅ ገበሬዎቻቸውን ከይዞታቸው የሚያፈናቅሉ መንግስታትም፤ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሣስቧል።

መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፤በመንግስታት ወኪሎችና በተመራማሪዎች በተከናወነውና 17 ወራት በፈጀው በዚህ ጥናት፤ በ25 አገሮች የሚኖሩ የ 350 ገበሬ ማህበራት አስተያዬት መካተቱ ተገልጿል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በሚሊየኖች የሚቆጠር ለምና ሰፋፊ እርሻ ለሃብታም ሃገራት ባለሃብቶች በርካሽ ዋጋ ሲቸበችብ መቆየቱ፣ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸው እንደተፈናቀሉ፣ ለርሃብና ለችግርም እንደተዳረጉ መዘገባችን ይታወሳል።

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ እየፈፀመ ስላለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ ይፋ ላደረገው የቢቢሲ መርማሪ ጋዜጠኞች ቡድን አስተያዬታቸውን በሰጡት በሶስት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፤ ላይ የውንጀላ ዘመቻ መክፈቱ ተዘገበ። የሰብዓዊ መብት ጥሰቱንም ” የደርግ ርዝራዦች የሚያናፍሱት የፈጠራ ወሬ ነው” ሲል ማጣጣል ጀምሮአል

የወያኔ አገዛዝ ከምዕራባዊያን ለጋሾች የሚቀበለውን የዕርዳታ ገንዘብ እንዴት አድርጎ የፖለቲካ ሥልጣኑን ዕድሜ ለማራዘም የሚያስችል ድጋፍ እንደሚገዛበትና ተቃዋሚዎችንም ለማፈን እንደሚጠቀምበት ሀምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም በታዋቂው የቢቢሲ ቴለቪዝን ላጋለጡት የምርመራ ጋዜጠኞች ቢሮ ቃላቸውን የሰጡትን ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን፤ዶክተር መረራ ጉዲናንና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን “የአገርን መልካም ስም” ማጉደፍ“ በሚል ወንጀል፤ ዘመቻ የከፈተባቸው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ በመረጃ ይፋ የሆነውን የቢቢሲን ዘገባ እራሱ በሚቆጣጠራቸው ሬዲዮና ቴሌቪዝን ማብጠልጠል መጀመሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከላከልን ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት፤ በረሀብ፣ በድህነት፣በዲሞክራሲ እጦትና፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት የምትታወቀውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስኬታማ ባልሆኑ መንግስታት(ፌይልድ ስቴትስ) ተርታ እየተመደበች ስላለችው አገራችን የሚያውቁትን በአደባባይ የሚናገሩ ተቃዋሚዎችን “የአገርን መልካም ስም በማጉደፍ ተግባር ተሰማርተዋል” በማለት የሚከሳቸው የመለስ በረከት አገዛዝ “ጎደፈ ስለሚባለው መልካም ስም” የሰጠው ዝርዝር ግን የለም። ቢቢሲን የመሰሉ አለም አቀፍ ከበሬታና ታማኝነት ያላቸው ሚዲያዎች የሚያወጡዋቸው ዜናዎችና ዘገባዎች ከዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍል እስከ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን በቀላሉ የሚደርስ በመሆኑ የተደናገጠው የወያኔ ቡድን የሚይዘውንና የሚጨብጠውን በማጣቱ ምስክርነታቸዉን ለቢቢሲ የሰጡትን ዜጎች “የደርግን ስርዓት ለመመለስ የሚሰሩ” ብሎ እስከ መወንጀል መድረሱ ብዙዎችን አስገርሞአል።

የደርግ ሥርዓት ከወደቀ ከሃያ አመት ቦኋላ ወያኔ አሁንም ለውጥ ፈላጊዎችን በደርግ ሥርዓት ናፋቂነት መክሰሱ ምናልባት ሰሞኑን ከወደ ዚምባብዌ በህይወት መኖራቸውን ከመግለጽ ላላለፈ ጉዳይ ድምጻቸውን በአንድ ሬዲዮ ጣቢያ ያሰሙት የቀድሞው አምባገነን መንግሥቱ ሃይለማሪያም መልዕክት ሌላ ተጨማሪ ሽብር ፈጥሮበት ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ አሳድሮአል።

በኢትዮጵያ ደሃ ህዝብ ገንዘብ የሚተዳደረው ሚዲያ ሰሞኑን በቢቢሲ ላይ ስለተከፈተው ዘመቻ አስተያየታቸውን የሰጡት ፕሮፌሰር በየነ ጰጥሮስ “ይህ ሰሞኑን በወያኔ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የምንሰማው ማስተባበያ «ችግሮችን ለመሸፈን የሚደረግ ከንቱ ፕሮፖጋንዳ ነው» በማለት አጣጥለውታል፡፡

«የምንለው በሬ ወለደ አይደለም በምርጫ ስለተሸነፍንም አይደለም፡፡ ሕዝባችን በረሃብ እያለቀ መሆኑን ስላረጋገጥን ነው፤» ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ ዕርዳታ- በመንግሥት መዋቅር ቁጥጥር ሥር በመሆኑ ለፖለቲካ መሣርያነት እየዋለ እንደሆነ በደቡብ የሚገኙ በርካታ ቦታዎችን በመጥቀስ እርግጠኛነታቸውን በድጋሚ ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም በአገራችን እየተፈጸመ ስላለው ሰቆቃ ያጋለጠው ዶክመንተሪ ከመሰራቱ በፊት፤ ጋዜጠኞቹ ሲያነጋግሩዋቸው በእርዳታ እየተቀጡ ካሉ ደጋፊዎቻቸው ያገኙትን መረጃ ተመርኩዘው ለቢቢሲ ጋዜጠኞች መንገራቸውንና ወደስፍራዎቹ ሄደው በራሳቸው መንገድ እንዲያጣሩ ጥቆማ መስጠታቸውንም ፕሮፌሰር በየነ አልሸሸጉም።

ፕሮፌሰር መስፍን በበኩላቸው፣ «መንግሥት በእኛ ላይ የሚያቀርበው ወቀሳ ምንም አይደለም፡፡ የሚያሳዝነው ግን ትችት ተቀብሎ ችግሩን ከማስተካከል ይልቅ፤ማን ምን አለ? ወደሚል ጨዋታ መግባቱ ነው»ብለዋል።

በአገሪቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስመልክተው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ለሚመለከታቸው አካላት አቤቱታ እያቀረቡ መሆናቸውን የገለጹት ፕሮፌሰር መስፍን፤ ለፍትህ ሲሉ የሚሠሩትን ሥራ በማጣመም ባለሥልጣናቱ “መንግስቱ ሀይለማርያምን ለማስመለስ ነው የሚሰራው” ማለታቸው እንዳሳዘናቸው ገልፀዋል።

ፕሮፌሰሩ አክለውም፡-«ሌላ አገር ቢሆን፣ እንዲህ ዓይነት ትችት ሲቀርብ ችግሩን ተቀብሎ አጣራለሁ፣ አስተካክላለሁ ነበር የሚባለው፤ በእኛ ላይ የሚያደርጉት ውርጅብኝ መቼም የሚቀር አይሆንም፡፡ አገሪቷን ግን እየገደሏት ነው፡፡ የያዙት ነገር ስለማያዋጣ፤ሌላ መንገድ ቢከተሉ ነበር የሚሻላቸው፤» ብለዋል።

## በዘረኛው አገዛዝ በጥናት ላይ ያልተመረኮዘ የዘመቻ ስራ፣ የትግራይ አርሶ አደሮች እጅግ መማረራቸው ታወቀ

በትግራይ ክልል የሚገኙ አርሶ አደሮች ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የውሃ ማቆር በሚል ከበርካታ አመታት ጀምሮ መተግበር አለባችሁ ብሎ በግዳጅ የጀመረው ዘመቻ ውጤታማ አለመሆኑና አርሶ አደሮችም በዚህ የግዳጅ ዘመቻ ክፉኛ መማረራቸውን የጀርመን ራዲዮ ጣቢያ ዶቼቨለ ዘገበ።

እንደ ዶቼቨለ ዘገባ ገበሬዎቹ በሰጡት አስተያየት ከላይ የወረደ መመሪያ ነው ተብሎ የተጫነባቸው የውሐ ማቆር ሥራ ጉልበት ከማባከን በስተቀር አንድም ጥቅም እንዳላስገኘላቸው መናገራቸውና፣ ይልቁንም ለዚሁ ሥራ ተብሎ የታደለውን ላስቲክ ለታሰበለት የውሐ ማቆሪያ ሳይሆን ለቤት ክዳንና ሌሎች ግልጋሎቶች ማዋላቸውን አስታውቀዋል ብሉአል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሥራው ውጤታማ ያልሆነበት ምክንያት በቂ ጥናት ተደርጎ ባለመጀመሩ መሆኑን በወቅቱ በዚህ ስራ ላይ የተካፈለ አንድ የእርሻ ልማት ሰራተኛ መናገሩ ታውቁአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ፣ ከምእራባዊያን ሃገራት የሚያገኘውን ድጋፍ ላለማጣት “አድርግ” የተባለውን ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታና ጥናት እንደወረደ በኢትዮጵያዊያን ላይ ሲጭን እንደቆየ በስፋት የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህ የውሃ ማቆር ስራ ዘመቻ በትግራይ ክልል ብቻ ሳይሆን በበርካታ የሃገሪቱ ክፍሎች በግዳጅ እንዲሰራበት ተወስኖ ምንም ውጤት ሳያመጣ የቀረና በርካታ ሚሊየን ዶላር በአየር ላይ እንዲበተን ያደረገም እንደነበር ፤በዚህ የውሃ ማቆር ስራ ላይ ተሳታፊ የነበሩ ባለሙያ ከሰጡን አስተያየት ለመረዳት ተችሉአል።

## ሰሞኑን በጋዜጠኞች ላይ የጭካኔ በትሩን ያነሳው አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ይህን እኩይ ተግባሩን በኢንተርኔት ካፌዎችና ተጠቃሚዎች ላይ መቀጠሉ ተዘገበ

አዲስ ነገር ኦን ላይን በመባል የሚታወቀው ድረገጽ እንደዘገበው ሰሞኑን ክፉኛ ይቃወሙና ይተቹት በነበሩ ጋዜጠኞች ላይ የጭካኔ በትሩን ያነሳው አፋኙ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የኢንተርኔት ካፌዎች ላይ ፊቱን ማዞሩ ታውቁአል። እንደ አዲስ ነገር ዘገባ፣ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ወራት ወዲህ የስለላ ሃይሎቹ በሙሉ አቅም ተሰማርተው በኢንተር ኔት ካፌዎች ላይ ጥብቅ ክትትል ሲያደርጉ እንደቆዩ የታወቀ ሲሆን፣ የአዲስ ነገር ሪፖርተር ከአዲስ አበባ እንደገለጸው ባለፈው ሳምንት ኢንተርኔት ካፌ ውስጥ ሆኖ አገዛዙን የሚቃወሙ ድረገጾችን ይመለከት የነበረን ተጠቃሚ ድረገጾቹን እንዳያነብና እንዲዘጋቸዉም ሲያስጠነቅቁት፣ በትዝብት መመልከቱን ገልጹአል።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሌላ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ግለሰብ በዘረኛው አገዛዝ ሶስት ታጣቂ ሃይሎች ከኢንተርኔት ካፌ እንዲወጣ መደረጉና ፕሮክሲ ሰረቨርን በመጠቀም ጸረ ሰላም የሆኑ መረጃ ድረ ገጾችን ማንበብ ወንጀል እንደሆነና በሃገሪቱ ህግም እንደሚያስቀጣ ገልጸው ከከባድ ማስጠንቀቂያ ጋር እንደለቀቁትም ታውቁአል። እንዲህ አይነት ተግባራት በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ከተሞችም ተስፋፍተው ያሉና እየተተገበሩ መሆናቸውንም አዲስ ነገር አክሎ ዘግቡአል።

ባለፈው ማክሰኞ አራት ኪሎ የሚገኙ ሁለት የኢንተርኔት ካፌዎች መዘጋታቸውንና ባለቤቶቹም ወደ እስር ቤት መወሰዳቸውን የዘገበው አዲስ ነገር፤ እነኚህን የካፌ ባለቤቶች ወደ እስር ቤት የወሰዱ ማንነታቸውን ቀይረውና የሲቪል ልብስም ለብሰው ሲሰልሉ የነበሩ የደህንነት ሰራተኞች መሆናቸውን ገልጹአል። በኢንተርኔቱ ውስጥ የነበሩት ኮምፒዩተሮችም በፖሊሶች መወሰዳቸውን፣ የኢንተርኔት ካፌ ባለቤቶቹም የተያዙት ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ ወንጀል ሰርታችኋል በሚል እንደሆነም ፖሊሶች መናገራቸውም ተያይዞ ተገልጹአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አሁን እየፈጸመ ያለው ድርጊት ጭራሹኑ ዘግናኝና ህዝብን ዝቅ አድርጎ ከማየትም ያለፈ እንደሆነ አስተያየታቸውን ለአዲስ ነገር ዘጋቢ የገለጹ ግለሰቦች ቀደም ብለው በፖሊስ የተወሰዱት የኢንተርኔት ካፌ ተጠቃሚዎችና ባለቤቶች የት እንደደረሱ እንደማያውቁም መናገራቸው ታውቁአል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ባሁኑ ሰአት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የወቅቱ የጥቃት ኢላማዎች ኢንተርኔት ካፌዎች መሆናቸው በስፋት እንደሚታወቅ ተገልጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና መከራ ሞልቶ ከፈሰሰ ጊዜያቶች የተቆጠሩ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያዊያን የአገዛዙ የፕሮፓጋንዳ ማሺኖች ከሆኑት የቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስርጪቶች ውጪ ምንም አይነት አማራጭ መረጃ እንዳያገኙ ለማድረግ ሌት ከቀን እየሰራ እንደሆነ በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz

እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org